# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 19 ህዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## የወጣቶች ተቀዳሚ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎቻቸው



# ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሁላችንም ትኩረት ይሻሉ

ከፍተኛ  የትምህርት ተቋማት ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች ያለፈውን ትውልድ እውቀትና ተሞክሮ በሥርዓት ጠብቀው በማቆየት ለአሁኑ ትውልድ የሚያስተላልፉ፤ የአሁኑ ትውልድ እውቀትና ተሞክሮ ደግሞ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚያቆዩ የእውቀትና ልምድ ማከማቻዎች ናቸው። ከፍተኛ የትምህት ተቋማት በምርምር ማዕከልነታቸው የአዳዲስ እውቀቶችና ክህሎቶች መገኛ ናቸው፤ የቀድሞ እውቀቶች ወቅታዊነት መፈተሻ ቦታዎችም ናቸው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እውቀትን ለተማሪዎቻቸው ብቻ ሳይሆን ለመላው ማኅበረሰብ የሚያሰራጩ ማዕከላት ናቸው።

ከእነዚህ ሁሉ በተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሲቪክ ባህል መገንብያ ማዕከላት ናቸው። የተለያዩ ሀሳቦችንና እይታዎችን አመዛዝኖ፤ የተቃረኑ እይታዎችን በጥሞና አዳምጦ ከተቃረኑ እይታዎች የሚጠቅመውን ወስዶ የራሱን እውነት የሚፈልግ ትውልድ የሚወጣው ከነዚህ ተቋማት ነው።

ወጣቶች በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሚያሳልፏቸው ዓመታት በትዕግስት ማድመጥን፤ በአስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን በባህልና በእምነት ከማይመስሏቸው ሰዎች ጋር አብሮ መኖርን፤ ሰዎችን ማሳመንን፣ ማኅበራትን ማደራጀትና መምራት የሚለማመዱት ጊዜ ነው። ወጣቶች ከጠባብ የቤተሰብ ወይም የሠፈር  ክልል ወጥተው ሰፊ የግኑኝነት ትስስር የሚፈጥሩት በዚህ የዩኒቨርስቲ ቆይታቸው ወቅት ነው፤ የግኑኝነት አድማሳቸው ሀገርን ተሻግሮ ዓለም ዓቀፍ ይዘት እንዲይዝ የሚያደርጉትም በአብዛኛው በዚህ ወቅት ነው።

በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን ያሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት መከወን ተስኗቸዋል። ዩኒቨርስቲዎቻችን የተለያዩ ሀሳቦች ተፋጭተው ሀቅ ነጥሮ የሚወጣባቸው ከመሆን ይልቅ ተነጋግረው የማያውቁ ወጣቶች በዘርና በሀይማኖት ተቧድነው የሚደባደቡባቸው ሜዳዎች ሆነዋል። የከፍተኛ ትምህት ተቋሞቻችን የሲቪክ ባህል የሚዳብርባቸው ከመሆን ይልቅ ጉልበተኛው ደካማውን የሚያጠቃባቸው እየሆኑ ነው። ዩኒቨርስቲዎቻችን ወጣቶች አመራርንት የሚማሩትባቸው ሳይሆን ጡንቻዎቻቸውን የሚፈትሹባቸው ሜዳዎች ሆነዋል።

ይህ ጉዳይ ሁላችንንም ሊያሳስበን ይገባል። ይህ የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ አይደለም፤ የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ነው።  የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሰዋዊ ከባቢ (human environment) የመቀየር ቀዳሚ ኃላፊነት መውሰድ የሚኖርባቸው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ራሳቸው ናቸው። የዩኒቨርስቲ ሕይወት ተመልሶ የማይገኝ ውድ የእድሜ ክፍል ነው፤ ይህን ጊዜ ማባከን ከወጣትነት አጭር  እድሜ ላይ እጅግ ምርታማውን ክፍል ማጣት ነው። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወጣት ይህን መፍቀድ የለበትም።  የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን የርስ በርስ ግንኙነት ጤናማ ለማድረግ ከራሳቸው ከተማሪዎች በላይ አቅም ያለው አካል የለም። የተማሪዎችን የርስ በርስ መልካም ግኑኝነቶችን የሚያደፈርሱ ጥቂቶች ናቸው፤ እነዚህን ደግሞ ተማሪዎች ያውቋቸዋል።  አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በእነዚህ ጥቂቶች ሳቢያ ሕይወታቸው እንዲበላሽ መፍቀድ የለባቸው። ብዙሀኑ ተማሪዎች የርስ በርስ ግኑኝነት ማዳበሪያ ክበባትን በማደራጀት፤ በክበቦቻቸው አማካይነት ጥቂቶቹን በሁሉም ረገድ መብለጥ ይጠበቅባቸዋል።

ቀጣይ ኃላፊነት ያለው በመምህራን ላይ ነው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን የአካዳሚ ትምህርት መምህራን ብቻ  አይደሉም፤ እያንዳንዱ መምህር  የሕይወት ክህሎቶችንም (life skills) ማስተማር እንደሚጠበቅበት ማወቅ ይኖርበታል።  የተማሪዎች ግለስብዕና ልማት (personal development) ከአካዳሚ ትምህርቶች ያላነሰ ዋጋ ያለው መሆኑ የአካዳሚው ማኅበረሰብ ሊገነዘብ ይገባል። ወላጆችን ሌላውም ማኅበረሰብ በዚህ ጉዳይ ላይ የየበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ይጠበቅበታል።

መንግሥት አጥፊዎችን በቸልታ የሚያልፍበት አግባብ ሥርዓት-አልበኝነትን እያበረታታ እንደሆነ ልብ ሊል ይገባል። ተማሪዎች ከጉልበተኞች ጥበቃ ይሻሉ፤ የድረሱልን አቤታቸው ሊደመጥ ይገባል። ችግሮች ደርሰው፤ የሰው ሕይወት አልፎ ወይም አካል ጎድሎ ብዙ ጉዳት ከደረሰ በኋላ ብቻ አይደለም መንግሥት እንዲደርስ የሚፈለገው። መንግሥት እንዲደርስ እንዲኖር የሚፈለገው አደጋዎች ከመድረሳቸው በፊት ነው።  መንግሥት አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት የመድረስ ብቃቱን ሊያሻሽል ይገባል፤ በአጥፊዎች ላይ የያዘውንም ለዘብተኝነት ችግሮቹ ደግመው ደጋግመው እንዲፈጠሩ በር ከፍቷል።የሄንን ግንዛቤ ውስጥ በመክተት አጥፊዋችን በመለየት ተገቢውን የህግ እርምጃ ሊወስድ ይገባለ።

# የፊታችን ቅዳሜና እሁድ ቀጠሮ የተያዘላቸው የሀገር ውስጥ ክንዋኔዎች











## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)


ህዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የወጣቶች ተቀዳሚ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎቻቸው

ከአለም ህዝብ 30 ከመቶ የሚሆነው ወጣት ነው። በተለይ በታዳጊ ሀገሮች፣ ወጣቶችና ህፃናት አብላጫውን ቁጥር ይይዛሉ። ወጣቶች የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ኃይል ናቸው። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትርጓሜ መሠረት ወጣት ማለት እድሜው ከ15 እስከ 24 ዓመት የሆነው ነው። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ከራሱ ሀገር ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ የራሱ የሆነ ትርጓሜ ሊኖረው ይችላል። በአፍሪካ የወጣቶች ቻርተር ትርጉም መሠረት ከ15-35 እድሜ ያለው ወጣት ተብሎ ስያሜ ይሰጠዋል፡

ኢትዮጵያም የሌሎችን ሀገራት ልምድና ውስጣዊ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወጣቶች ፖሊሲ ላይ ወጣት ማለት ከ15- 29 የሚገኝ እንደሆነ ገልፃለች። ለዚህ ገደብም በብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ማብራሪያ ላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

15 ዓመት የሀገራችን የወጣት እድሜ ገደብ መነሻ የሆነው የሀገራችን የሥራ ስምሪትን ከግምት በማስገባት፣ በአብዛኛው የዚህ እድሜ ለአካለ መጠን የመድረስ በር በመሆኑ፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማጠናቀቅ የእድሜ ጣርያ በመሆኑና በተጨማሪም ከዚህ እድሜ በላይ ያሉ በአብዛኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አምራች ኃይል ውስጥ ስለሚካተቱ ነው።

29 ዓመት የዚህ የእድሜ ገደብ ጣርያ የመሆኑ ምክንያት ደግሞ የሀገራችንን የአንድ ሰው አማካይ የእድሜ ዘመን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር በዚህ እና ከዚህ እድሜ በላይ ያሉ ቤተሰብ የሚመሰርቱና አፍላነትን ያለፉ ሆነው ስለሚገመቱ፣ ወጣቶች መደበኛ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሥራ አለምን የሚቀላቀሉት አብዛኛው በአማካይ አመት በመሆኑ በርካታ ሠራተኛ ወጣቶችን ወደ ገደቡ ለማስገባት እንደሆነ ተጠቅሷል።

የሀገራችን ወጣቶች በሀገራችን ካለው ህዝብ ከፍተኛውን ቁጥር እንደመያዛቸው ተገቢውን ትኩረት እና የተሳትፎ እድል አልተሰጣቸውም። በዛው ልክም ንቁ ባለሙሉ ኃይል እና አምራች በመሆናቸው የአቅማቸውን ለሀገራቸው እንዲያበረክቱ እድሉ አልተመቻቸላቸውም።

## የሃገራችን ወጣቶች ችግሮች እና አንገብጋቢ ጥያቄዎች

### ፩) ሥራ - አጥነት

በሀገራችን በወጣቱ ዘንድ ትልቁ መሠረታዊ ጥያቄ ሥራ አጥነት ነው። ሥራ አጥነቱም በገጠርም ሆነ በከተማ የተስፋፋ ከፍተኛ ችግር ነው። ለኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሥራ አጥነት መሆን በርካታ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ሀገራችን የምትገኝበት ዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ነው። ዘርፎቻችን ካለን የህዝብ ቁጥር ጋር ያለመመጣጠናቸው፣ መደበኛ ያልሆኑ ዘርፎች በበቂ ሁኔታ ያለመዘጋጀታቸው፣ የግሉ ዘርፍ በበቂ ሁኔታ የሥራ እድል አለመፍጠሩ፣ በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የእርሻ መሬት እጥረት እና የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት ተጠቃሽ ናቸው። ወጣቶች በተሳሳተ የትምህርት ፖሊሲ ምክንያት ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት ባለመቻላቸው፣ በምርጫቸውና በችሎታቸው አለመማራቸው ለሥራ አጥነትና ከደረጃ በታች (Under Employment) ለመቀጠር ሰለባ ሆነዋል።

በወጣቶች ዘንድ ሌሎች እንዲቀጥሯቸው መጠበቅ እና አዳዲስ ሥራ እና ሃሳቦችን ያለማመንጨትና ሥራ የመፍጠር ተነሳሽነት ያለመኖር ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው።

### ፪) ስደት

በሀገራችን ያለው ከፍተኛ ኢኮኖሚ ድቀት እና ሥራ አጥነት ምክንያት ወጣቶች የተሻለ ኑሮ እና ስራ ፍለጋ፣ ከራሳቸውም አልፈው ቤተሰቦቻቸውን ለመደጎም በከፍተኛ ቁጥር ይሰደዳሉ። ገጠር ያሉ ወጣቶች ወደከተማ ይፈልሳሉ። በተጨማሪም በህገ ወጥም ሆነ በህጋዊ መንገድ ድንበር አቋርጠው የተሻለ ህይወትን ይገኝበታል ወዳሉት ቦታ ይሰደዳሉ።

### ፫) ጤና

ወጣቶች በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ሁኔታ የተለያዩ የጤና ችግሮች አሉባቸው። በተለይ ኤች አይ ቪ እና የአባላዘር በሽታዎች ወጣቱን በማጥቃት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። ለዚህም ዋነኛ መነሻ ምክንያቱ በቂ የሆነ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ አለመሰራቱ ነው። ወጣቶች አፍላ በመሆናቸው ሁሉንም አስደሳች የሆኑ ነገሮች የመሞከር ፍላጎት እና ኃይል አላቸው። ይህ ኃይል እና ፍላጎት ነገሮችን ሳያመዛዝኑ እንዲያደርጉ ይገፋፋቸዋል።

ሌላው ከፍተኛ ችግር በሴት ወጣቶች ላይ የሚያጋጥመው ችግር ያልተፈለገ እርግዝና እና የወጣት እናቶች ሞት ነው። የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ባለመስፋፋቱ በወጣቶች ቅድመ ጥንቃቄዎች አይደረግም፡ ፡ በተጨማሪም እርግዝናን ጤናማ ባልሆነ መንገድ ለማስወረድ ስለሚሞከር በርካቶች ህይወታቸውን ያጣሉ። ስለዚህም የስነ ተዋልዶ ጤና ግንዛቤ በወጣቱ ዘንድ በእጅጉ መስፋፋት ይኖርበታል።

### ፬) ንቁ ፖለቲካዊ ተሳትፎ

ወጣቶች ቀደም ባሉት ስርዓቶችም ሆነ አሁን ባለንበት ጊዜ የለውጥ፣ የመብት መከበርን እና የእኩልነት ጥያቄን ሲያስተጋቡ የነበሩ እና በስርዓቶቹም የጥቃት ኢላማ ሲደረጉ የነበሩ ናቸው። ነገር ግን ያለን የፖለቲካ ስርዓት ወጣቶችን በውሳኔ ሰጪነት እና በአመራርነት በብዛትና በበቂ ሁኔታ ሲያሳትፍ አይታይም። በተለይ በቅርብ ከሽግግሩ በፊት

በነበረው የኢህአዴግ አስተዳደር ወጣቶችን ለፖለቲካ ስልጣን እንደጠላትና ተጋፊ በማየት ሆን ተብለው የተሰሩ ሴራዎች ነበሩ።

### ፫) ሱሰኝነት

በአሁኑ ወቅት በተለይም በከተሞች የሚኖር ወጣት በተለያዩ አደንዛዥ ሱሶች ተገዢ መሆኑ አሳሳቢ ነው። ለሱሰኝነት መንሰራፋት ሥራ አጥነት ያስከተለው መሄጃ ማጣትና ተስፋ መቁረጥ እንዲሁም በእፆች ላይ በቂ ቁጥጥር አለማድረግ አስተዋፅዖ እንዳደረጉ ይታመናል።

## ለዛሬዋ እና ለነገዋ ኢትዮጵያ ምን አይነት ወጣቶች ያስፈልጓታል?

እንደ ሀገር የወጣቶች ሚና ለዴሞክራሲያዊነት፣ ለሙያ፣ ለጥበብ፣ ለዕውቀትና ለክህሎት፤ ንቁና በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጹ ዜጎች እስካልሆኑ ድረስ ሀገር አለን ብለን ማውራት ጉራና ተራ ድፍረት ነው የሚሆነው :: “ሀብት በሃያ ዓመቱ፤ ሀሳብ በ60 ዓመቱ” አይነት ወጣት ለሀገርና ሀገረ - መንግሥት ግንባታ ያለው ፋይዳ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: በዚህ ሀሳብ ከተግባባን ቀጥሎ የሚመጣው ጥያቄ ወጣቱን በሁለንተናዊ መልኩ እንደት እናበልጽጋቸው? የሚለው ነው:: ሁሉም ባለድርሻዎች (ወላጆች፣ አሳዳጊዎቻቸው፣ አማካሪዎች፣ መንግሥት በህፃናትና በወጣቶች ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት ወዘተ) በኹለንተናዊ መልኩ ግብ ተክለው መሥራት ካልቻሉ ውጤቱ ግልፅ ነው:: ስለ ወጣቱ ባሰብን ቁጥር ወደ ኋላ ተጉዘን ከማኅፀን ጀምረን የማሰቡ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በተለይ በተለይ ከትምህርት ገበታ ጀምሮ ከፍተኛ ክትትል እየተደረገ በአካላም የጠነከሩ፣ በአዕምሮም የበሰሉ በምክንያት የሚያምኑ ወጣቶችን ማፍራት ይቻላል:: ወጣቶች በሚያደርጓቸው በእያንዳንዷ እንቅስቅሴዎች፣ ግንኙነቶችና ተሳትፎዎች ሁሉ በመካከላቸው ያለውን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ልዩነቶችን በሳይንስና በቴክኖሎጂ ታግዘው ለሰው ልጅ ሰላም እና ለሀገራችን እድገት መሥራት አለባቸው:: እንዲሁም በሀሳብ ደረጃ ያሉ የእርስ በእርስ እና ከሌላው አንፃር ያሉ ልዩነቶችን በፀጋ የመቀበል፣ በእኩል ዓይን የማየት፣ የመከባበር ባህልን እያዳበሩ፤ በሌላ በኩል እየተንከባለሉ የመጡ አሉታዊ ባህሎችን እያስወገዱ በኅብረት የመንቀሳቀስ ለጋራ ዓላማ፣ ራዕና ግብ በአንድነትና በፅናት መቆም፤ ለሕግ በላይነት ቅድሚያ መስጠት እና “የሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል!” የሚል አቋም ከወጣቱ ይጠበቃል :: ይህን የምንፈልገውን ወጣት አምራች ሃይል ለመጠቀም እና ሀገሩንም የሚጠቅም ለማድረግ መንግስትም ሆነ የሚመለከታቸው አካላት የሚከተሉትን ማድረግ ይገባቸዋል::

- ወጣቶች የፖለቲካ ተሳትፏቸው እና አመራር ሰጪነታቸው እንዲጎለብትና እንዲበዛ፣ በእጃቸውም ያለውን የአምራችነት ኃይል ለሀገራቸው እንዲያበረክቱ፡ የወጣቶችን የአመራር ብቃት የሚያጎለብቱ ስልጠናዎችን ማካሄድ፣ የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ጥናቶችን በማጥናትና ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ፣ ወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የሚያሳይ በፆታና በዕድሜ የተለየ መረጃ እንዲያዝና እንዲደራጅ ማድረግ፣ ሴክተሮች በሚያካሂዷቸው የግንዛቤና ንቅናቄ ሥራዎችን የወጣቶችን ጉዳይ ትኩረት በመስጠት መንቀሳቀስና የህብረተሰቡን አመለካከት መለወጥ፣ ሴክተሮች በሚያደርጓቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች የወጣቶች አደረጃጀቶች ማሳተፍና በቅንጅት መስራት፣ በእጅጉ አስፈላጊ ነው::
- ወጣቶች እንዲደራጁ፣ በተለያየ ዘርፍ ራሳቸውን ያበቁ ወጣቶችን ከሌሎች ጋር በማቆራኘት ልምድ እንዲቀስሙና እንዲነቃቁ ማድረግ፣ አጫጭር ሥልጠናዎችንና የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፣ በሀገራቸውና በግላቸው ጉዳይ እንዲመክሩበት፣ እንዲሳተፉ፣ እንዲወስኑ፣ እንዲጠቀሙ፣ ጥሩ ተመሪና ጥሩ መሪ እንዲሆኑ ጥረታቸውንና ፍላጎታቸውን ከቀዳሚው ትውልድ ልምድና ተሞክሮ ጋር በማስተሳሰር በመደገፍ የተጣለባቸውን ታሪካዊ አደራ በብቃት እንዲወጡ የቢሮክራሲውን በር ወገግ አድርገው መክፈትን ይጠበቃል ::
- የወጣቶችን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲ መንደፍ፤ ለወጣቶች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የመልካም አስተዳደር፤ በልማት ግንባታ ሂደቶች ውስጥ በተደራጀ አኳኋን ተሳትፎ አድርገው ከልማቱ በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ልዩ ትኩረት ለሚሹ ወጣቶች ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው መሥራት፣ የወጣቶችን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲ መንደፍ፤ ለወጣቶች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የመልካም አስተዳደር፤ በልማት ግንባታ ሂደቶች ውስጥ በተደራጀ አኳኋን ተሳትፎ አድርገው ከልማቱ በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ወጣቶች ከስሜታዊነት ተላቅቀው ዴሞክራሲንና ፍትሕን እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት በመሳተፍ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማስፋፋት፣ የሥልጣን ብልግናንና ሙስናን እንዲሁም አምባገነንነትን የሚዋጉ ወጣቶች/ዜጎች ፣ በራስ መተማመን ላይ እንዲደርሱ መሥራት የመንግስትና ከሌሎች ባለድርሻዎች የሚጠበቅ ተግባር እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል ።

በወጣቶች ላይ የሚደርሱ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ የኃይል ጥቃቶች ለማስወገድና የህገወጥ ዝውውርን ለመግታት የየድርሻ ኃላፊነት መወጣት፣ የወጣቶችን ጉዳይ በተመለከተ ከወጣቶች ጉዳይ አካላት ጋር በትብብርና በአጋርነት መስራት አስፈላጊ ነው:: በዚህ ረገድ በእያንዳንዱ ሴክተር ውስጥ ወጣቶችን ትኩረት እንደተሰጣቸው በበቂ ሁኔታ መወከላቸውን እና የሚሠሩት እያንዳንዳቸው ስራዎች ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ኢዜማ ያለወጣቶች ተሳትፎ፡ በቂ ውክልና እና ተጠቃሚነት የሀገራችን እድገት እና ዴሞክራሲያዊነት ማሳካት እንደማይቻል ያምናል:: ለዚህም ነው በፕሮግራሙ ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ያካተተው እና ፖሊሲም እያዘጋጀ የሚገኘው:: ወጣቶች ላይ መሥራት ልዩ ትኩረት የሚያሻው በመሆኑ በሥራ አስፈፃሚ ውስጥ ሁለት የወጣት ተጠሪዎች ከማኖሩም በላይ የወጣቶች ቋሚ ኮሚቴ በማቋቋም ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲፈቱና መፍትሄ እንዲመጡ በመስራት ላይ ይገኛል::

## ኢዜማ በደቡብ ጎንደር ህዝባዊ ውይይት አካሄደ

ኅዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ሕዳር 07 ቀን 2012 ዓ.ም በደቡብ ጎንደር ዞን፣ በደብረ ታቦር ከተማ በዞኑ መሰብሰበቢያ አዳራሽ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታና የኢዜማን አደረጃጀት በተመለከተ ህዝባዊ ውይይት ማካሄዱን የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

በደብረ ታቦር ከተማ የኢዜማ አባላትና አመራር፣ የሌሎች ፖለቲካ ፓርቲ አባላት እንዲሁም የመንግስት አካላት በተገኙበት ሕዝባዊ ውይይት ላይ ስለ ኢዜማ መዋቅር፣ ከወረዳ ጀምሮ ስላለው አደረጃጀት፣ ወረዳዎች ራሳቸውን እንዴት አድርገው በአቅም ማደራጀት እንዳለባቸው የተብራራ ሲሆን፤ በፖርቲው አሠራር ላይ ጠርተው ያልወጡ ጉዳዮችን ለተሰብሳቢዎቹ ግልጽ በማድረግ ኢዜማ አሁን አለኝ የሚለውን አማራጭ በማቅረብ በ2012 ዓ.ም ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው ሀገራዊ ምርጫ ላይ እንደሚወዳደር ለጉባዔው ታዳሚዎች ተገልጿል፡፡

“በሀገራችን ላይ ሰላም ሳይኖር፤ ዜጎችም በየጊዜው እየተገደሉ እንዴት ምርጫ ይካሄዳል?” የሚል ጥያቄ ከውይይቱ ተሳታፊዎች የቀረበ ሲሆን “በተደጋጋሚ ቅድሚያ ለሰላም መስጠት እንዳለበት ስንናገር ቆይተናል፤ ሰላም ማስከበር የመንግስት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኃላፊነት ነው ብለን እናምናለን፡፡ ለዚህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሰላምን ለማስፈን አስፈላጊውን ስራ እንሰራለን፡፡ ከዚህ ባለፈ ምርጫ ይኖራል ከተባለ ግን ግዴታ ወደ ምርጫው እንገባለን” በማለት የኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ለተሰብሳቢዎቹ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሊቀመንበሩ ሕዝባዊ ስብሰባው የተሳካ እንዲሆን አስተዋፅኦ ተጫውተዋል ላሏቸው ለደቡብ ጎንደር ፀጥታ አካላት፣ ለከተማው አስተዳደር፣ ለከንቲባው፣ በተጨማሪም ለጋፋት ሆቴል ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

## ኢዜማ በ22 ዞኖች ምርጫ 2012 አስመልክቶ ለአባላቱ እና አመራሮቹ የመጀመሪያ ዙር ስልጠና ሰጠ

ኅዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ባሳለፍነው ሳምንት አዲስ አበባን ጨምሮ በ22 ዞኖች ከ310 በላይ የምርጫ ወረዳዎችን ያሳተፈበት ስልጠና በስኬት ማጠናቀቁን የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

በሀገር ውስጥ ባሉ ኢዜማ ባደራጃቸው ዞኖችና ወረዳዎች በአንድ ጊዜ፣ በተመሳሳይ ሰዓትና ቀን የተሰጠው ሥልጠና ዋና ትኩረቱን ያደረገው በቀጣዩ ምርጫ ላይ የኢዜማ አባሎችና አመራሮች ሊያደርጉት ስለሚገባ ቅድመ ዝግጅትና ሊከውኗቸው ስለሚገባ ሥራዎች ነው፡፡

“ስልጠናው ለአምስትና ለስድስት ወራት ያህል ኢዜማ ሲሰራ የነበረው ሥራ በተግባር የተፈተሸበት እንደሆነ፤ አልፎም ተርፎ ትልቅ ድርጅት እየገነባን መሆኑን ያስመሰከርንበት ነው” በማለት የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ገልጸዋል፡፡ በተሰጠው ስልጠና የኢዜማ የዞን አስተባባሪዎችና የምርጫ ወረዳ አመራሮች በተገቢው መንገድ ሥራቸውን እየሠሩ መሆኑን ማረጋገጥ እንደተቻለና በቅርብ ጊዜ ውስጥ በአሁኑ ዙር ያልተካተቱ ዞኖችና የምርጫ ወረዳዎች በማካተት ስልጠናው ተደራሽ እንደሚደረግ ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

## ኢዜማ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የሙያ ማሕበራት ጋር የሚወያይ ይሆናል

ሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የሙያ ማኅበራት ቋሚ ኮሚቴ የፊታችን ቅዳሜ ሕዳር 13 ቀን 2012 ዓ.ም ከተለያዩ የሙያ ማሕበራት ተወካዮች ጋር በሰሜን ሆቴል ከጠዋቱ 3፡00 ጀምሮ ውይይት እንደሚያደርግ የኢዜማ የሙያ ማኅበራት ተጠሪ እሌኒ ነጋሽ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

“ይህን ውይይት ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?” በሚል ከዜጎች መድረክ ለተነሳላቸው ጥያቄ ተጠሪዋ ሲመልሱ የኢዜማ ሙያ ማሕበራት ቋሚ ኮሚቴ ለሙያ ማሕበራት ትኩረት በመስጠት ስራ ሲሰራ እንደነበር ጠቁመው፣ እስካሁን ድረስ ቋሚ ኮሚቴው ሲያደርገው የነበረው እንቅስቃሴና የከወናቸው ስራዎች ምን እንደሚመስሉ ገለፃ ለማድረግ እንዲሁም ከሌሎች የሙያ ማሕበራት ጋር ለመወያየት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮን) ጨምሮ 250 የሙያ ማሕበራት የውይይቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ እንደተደረገላቸው ተጠሪዋ ገልፀዋል፡፡

በእለቱ ከሙያ ማሕበራቱ ጋር በሚኖረው ውይይት የሙያ ማኅበራት ሚና ምን መምሰል አለበት በሚል ርዕስ የኢዜማ ሙያ ማሕበራት ተጠሪ እሌኒ ነጋሽ ለውይይት የሚሆን መነሻ ሀሳብ የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡ በተጨማሪነትም ሁለት ጥናታዊ ፅሁፎች በመድረኩ ላይ የሚቀርቡ ይሆናል፡፡

በአ.አ.ዩ የፖለቲካ ሳይንስ መምሕር የሆኑት ባንቲይገኝ ወርቁ “ILO in relation to Ethiopia” በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያቀርቡ ሲሆን ሌላኛው ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢ የሆኑት መምሕር ወንድወሰን ተሾመ ደግሞ “የኢትዮጵያ ሙያ ማሕበራት ታሪካዊ አመጣጥና ሚናቸው” በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያቀርቡ መሆኑን ለዜጎች መድረክ የደረሰው መረጃ ያስረዳል፡፡

በውይይቱ ላይ የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)፣ የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋና ሌሎች የፓርቲው አመራሮች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡